# የክብሩ ብርሃን ታላቅነት

## ከእጅጉ ረታ

ቤተ ክርስቲያን መታሰቢያነታቸውን በታላቅ ቁም ነገር ጠብቃ ከምታከብርላቸው በዓላት አንዱ በዓለ ደብረ ታቦር ነው ። ይህ ዕለት በጌታ ምድራዊ ሕይወት ውስጥ ከፍተኛ ድርጊቶች ከተፈፀሙባቸው ዕለታት አንዱ በመሆኑ ፣ አበይት ተብለው ከሚጠሩት ከተሰዓቱ በዓላተ እግዚእ ውስጥ አንዱ ነው ።

ነሐሴ 13 ላይ ይውላል ። በመሠረቱ በዓላት የሚከበሩት የተፈጸሙ ድርጊቶችን መታሰቢያነት ለማስታወስ ነው ። ደብረ-ታቦር የሚለው ስም ፣ ግን ድርጊቱ የተፈጸመበትን ቦታ ቢያመለክት እንጂ-ድርጊቱን ራሱን አያንፀባርቅም -የቦታ ስም ነው ። ጌታ ብርሃነ-መለኮቱን የገለጠበትን ይህን ዕለት ከእኛ በቀር ፣ ስሙን ደብረ ታቦር ብሎ - በቦታው ስም - የሚጠራው የለም ። በምስራቁም ሆነ በምዕራቡ የክርስትና ዓለም የሚታወቀው መለወጥ (ትራንስፊገሬሽን) ወይም በክብር መገለጥ ተብሎ ነው ።

ወንጌላውያን ስለ ጌታ ምድራዊ ሕይወት ባወሱበት ጊዜ ፣ ባጠቃላይ ክብደት የሰጡት ስለተፈጸሙት ድርጊቶች በመሆኑ ፣ ስለ ቦታ ስም እምብዛም የተጨነቁ አይመስልም ። ተራራ ፣ ከተማ ፣ ምድረበዳ እየተባሉ በወል በደፈናው የተጠሩ አያሌ ቦታዎች አሉ ። (ማቴ. 4. ቁ. 1 ። ማቴ 5፣1 ። ማቴ.14፣13 ማር. 1፣12 ። ማር. 3፣13 ። ሉቃ.6፣12 ። ሉቃ. 10፣38 ። ሉቃ. 11፣1) ወ.ዘ.ተ. ይሁን እንጂ ሥፍራዎቹ በዘመናት ጉዞ አልፈው ታሪካዊ መታሰቢያነታቸውን እንደያዙ እስከ ጊዜያችን ደርሰዋል ። ከእነዚህም አንዱ የታቦር ተራራ ነው የዚህ ተራራ ስም በሐዲስ ኪዳን መጻሕፍት ውስጥ በውል ተለይቶ አልተመለከተም ። መድኃኒታችን በክብሩ ብርሃን ሲገለጥ በቦታው ተገኝተው የዐይን ምስክር ከነበሩት አንዱ ቅዱስ ጴጥሮስ "ቅዱስ ተራራ" አለ እንጂ ሌላ ስም አልጠራም ። (2ኛ ጴጥ. 1 18) ሌላው ደቀመዝሙር ደግሞ ፡- እርሱም ወንጌላዊ ዮሐንስ በጭራሽ ስሙን አላነሳውም ፤ ታሪኩን አላወሳውም ።

ሲወርድ ሲዋረድ የመጣውን ታሪክ በመያዝ ግን ፣ የኦርቶዶክስና የላቲን አብያተ ክርስቲያናት ጌታ በባሕርየ መለኮቱ የተገለጠበት ቦታ የታቦር፡- ተራራ መሆኑን ያረጋግጣሉ ። በተራራው አናት ላይም አንድ ትልቅ የፍራንሲስካን ገዳም ለመታሰቢያ ተሠርቷል፡- መታሰቢያነቱም ከመካከል ያለው የጌታ ፣ በስተቀኝ ያለው የሙሴ ፣ በስተግራ ያለው የኤልያስ ነው ። አንድ መጠነኛ የሆነ የግሪክ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያንም እንደዚሁ አለ ። የታቦር ተራራ 1.929 ጫማ ከፍታ ያለው ደን የለበሰ ውበትና ግርማን የተጐናፀፈ የደስ ደስ ያለው ተራራ ነው ፡- ከጥንት ጀምሮ ምናልባት በዚህ ጭምር ሳይሆን አይቀርም ቅዱስ ጴጥሮስ ነሸጦት በዚያ መኖርን ያስመኘው ። በሌላ አንፃር ጌታ ብርሃነ መለኮቱን የገለጠው በአርሞንኤም (ሔርሞን) ተራራ እንጂ ምን ቢያግድ በታቦር ይሆንና ያሉ አሉ። ለዚህ ያደረሳቸውም መድኃኒታችን ክብሩን ከመገለጡ ከስድስት ቀን በፊት ሰዎች ማን ይሉኛል ? ብሎ ደቀ መዛሙርቱን የጠየቃቸው በቂሣርያ ዘፊልጵስ ሳሉ ነበርና ፣ የአርሞንኤም ተራራም ከዚችው ከተማ 20 ኪሎ ሜትር ርቆ በስተሰሜን ሲል በመሆኑ ወደ "ረጅም ተራራ" ይዟቸው ወጣ የተባለለት አርሞንኤም ለማለት ነው ብለዋል።የአርሞንኤም ከፍታው 9.232 ጫማ የሆነ ጉማም ፣ በራዳም ተራራ ነው ። ለኑሮ የሚስማማ ፣ የሚያስመኝም አይደለም ። ቅዱስ ጴጥሮስም እንዲህ ያለውን ቦታ ለኑሮ የተመኘው አይመስልም ። ብቻ ዋናው ቁም ነገር በብርሃነ መለኮቱ የመገለጡ ጉዳይ ስለሆነ ፣ ቦታው ያም ሆነ ይህ የሚያከራክር አይደለም ።

ጌታ የባሕርይ ክብሩ በሆነው በብርሃነ መለኮቱ የተገለጠው ያለ ምክንያት አልነበረም ። ይህ ከመሆኑ ከስድስት ቀን በፊት ከሐዋርያት ጋር በቂሣርያ ሳለ ፣ ስለእርሱ ማንነት ጠይቋቸው ሲመልሱለት አንዳንዶቹ ኤልያስ ፣ ሌሎቹም ከነቢያት አንዱ ነው ይሉሃል ብለውት ነበር ። ስለዚህ እሱ ሙሴ ወይም ኤልያስ አለመሆኑን ተረድተው ጥርጣሬአቸውን እንዲያስወግዱ ሙሴና ኤልያስን ከእርሱ ጋር አምጥቶ አሳያቸው ። እንዲሁም በሙሴ አሪት ፣ በነቢያት መጻሕፍት ስለእርሱ የተጻፈው ሁሉ መድረሱን መፈፀሙን እንዲረዱት ለማድረግ ነው ።

የዓለም መድኃኒት በባህርይ ክብሩ በተገለጠ ጊዜ ሦስት ታላላቅ ነገሮች ተፈጽመዋል ። የመልኩ መለወጥ ፤ የሙሴና የኤልያስ ከእርሱ ጋር መታየት ፣ አብ ስለ ልጁ የሰጠው ምስክርነት ።

ፊት (ገጽ) አንድ ሰው ማንነቱ ተለይቶ የሚታወቅበት የሰውነት ዋና ክፍል ሲሆን፣ ልብስም የአካል መሸፈኛ ነው ስለዚህ"...ፊቱም እንደፀሐይ በራ ፤ ልብሱም እንደ ብርሃን ነጭ ሆነ ተባለለት ። (ማቴ 17/2) ምሳሌው ወይም ማነጻጸሪያው ግን ፍጹም ፣ አይደለም ፤ ምሳሌ ዘየሐጽጽ ፡- መምሕራን እንደሚነግሩን ። መቼም ፀሐይ ብርሃኗ ዐይን ስለሚመዘምዝ (ስለሚበዘብዝ) ሙሉ በሙሉ ትክ ብሎ ሊያይዎት የማይቻል በመሆኑ ብቻ ፣ እናመሳስል ፤ እናነጻጽር ካልተባለ በስተቀር የፍጡር ብርሃን ከፈጣሪ ብርሃን ጋር በምንም ዓይነት ሊመሳሰል ሊነጻጸር እንዳይችል ግልጽ ነው ። ሙከራው የሰው አእምሮ ሊረዳው በሚችል ገንዘብ የተደረገ ማነጻጸሪያ እንጂ ፍጹምነት የለውም ። እንዲህ ነው ብሎ መግለጽ ያስቸግራል ።



ትንሣኤ ቁጥር 47 ነሐሴ 1973

www.ethiopianorthodox.org

ልዩ ብርሃን ነው፡- ለቅዱሳን በፀጋ ከሚሰጠውም ብርሃን የላቀ ነው ። ይህ ብርሃን ሙሴ ከሲና ተራራ ሲወርድ በፊቱ ላይ ከተሣለበት ብርሃንም ጋር ፈጽሞ አይመሳሰልም ፤ ልዩ ነው ። ሙሴ ፊቱን ሲሸፍን ልብሱ ብርሃኑ እንዳይታይ ፡ እንዲጋረድ ያደርገው ነበርና -የፀጋ ስለሆነ የበራውም ፊቱ ብቻ እንጂ መላ ሰውነቱ አልነበረም ። የዓለም ብርሃን ክርስቶስ ግን የተለወጠው ፤ ብርሃን የሆነው መላ-አካሉ፤መላ-ሰውነቱ እንጂ ፊቱ ብቻ አልነበረም ። በባሕርየ መለኰቱ ሲገለጥም ልብሱ ብርሃኑን ሰውሮ ሊያስቀረው አልቻለም።ልብሱ ራሱ እንደ ብርሃን ነጭ ሆነ እንጂ ። ይህ ብርሃን የክብሩ መንፀባረቅ ነውና (ልዩ ብርሃን) አማናዊ ብርሃን! መለኰታዊ ብርሃን !- -የብቻ ገንዘብ የሆነ፡እነሆ ይህ ፤ ብርሃን ፤ የባሕርይ ገንዘቡ የሆነ ፊት ነው ፣ በተሣልቆ ምራቅ የተተፋበት ፡ በድፍረት በጥፊ የተመታውም፤ለዚህ በክብር ለተገለጠ ፡ ራሱን በገዛ ፈቃዱ ስለኛ በደል አሳልፎ በመስጠት ውርደትንና ሕማምን ለተቀበለ አምላክ ወየ አንክሮ ይባላል ።

ከዘመነ ኦሪት ጀምሮ ደመና ጌታ በክብር የመገለጡ ፤ በረድኤት የማደሩ ምልክት መሆኑን መጻሕፍት ተባብረው ገልጸዋል ። አባቶችን ያነጋግራቸው የነበረውም በደመና ሆኖ ነበር ። (ዘጸአት 19/9 ። 34/5 ። ዘኁልቁ 11/25 ዜና መዋ ካልዕ 5/13 - 14 ። መዝ 98/6 - 7 ሕዝ. 1/4 ወ.ዘ.ተ.) እንዲሁም ወልደ ዕጓለ እመሕያው ክርስቶስ በኃይልና በታላቅ ክብር ሁለተኛ የሚመጣው በብሩህ ደመና ነው ። (ማቴ 24/30 ራዕ1.7) (በታቦር ተራራ የባሕርይ ክብሩን ለመግለጥ በፈለገ ጊዜ ፤"ብሩህ ደመና ጋረዳቸው ፤ ከደመናውም ውስጥ ከእርሱ ደስ የሚለኝ የምወደው ልጄ ይህ ነው ፤ እርሱን ስሙት ፤ " የሚል ቃል መጣ ። ይህ ድምፅ በውሃ ተጠምቆ ሲወጣ በዮርዳኖስ የተነገረ ቃል (ድምፅ) ነበር።ለአጽንዖተ ነገር እዚህ ላይ ተደገመ ። ማቴ. 3/17 የተሰማው ድምፅ ቀድሞ ጌታ በሲና ተራራ ሕግን ለሙሴ ሲሰጥ መብረቅና ነጐድጓድ የተቀላቀለበትን መለከት የተሰማበትን የመሰለ አስፈሪ ፤ ወይም ኤልያስን በኰሬብ ተራራ በተነጋገረው ጊዜ አውሎ ንፋስ ተንጦ ምድር ተንቀጥቅጦ እንደተሰማው ያለ አሸባሪ ድምፅ አልነበረም ። ደስ የሚያሰኝ ውብ ድምፅ ፤ ልዩ ቃና ያለው ለስላሳ ፡- የምወደው ልጄ ይህ ነው ፤ እርሱን ስሙት የሚል ። እርሱን ስሙት ያለው ቃሉን ስሙት ሲለን ነው ፤ ቃል የተባለም ራሱ ከአብ ዘንድ የወጣው አንድ ልጁ ጌታ ክርስቶስ ስለሆነ የዘለዓለም ድኅነት ይሆንልን ዘንድ በእርሱ ማመን ዮሐ/14/24 ። እርሱን (ቃሉን) መስማት ነው ። ባጠቃላይ በቅዱሳት መጻሕፍት የተነገረው ቃሉ የውነት ፤ የፍቅር ፤ የሰላም ፤ የደስታ ፤ የእረፍት ቃል ነው ። የመተሳሰብ የመረዳዳት ቃል ፡- የበጐነትን መንፈስ የተመላ ሕይወት የሚሰጥ እውነተኛ ቃል ነው ። (ዮሐ. 6/36) ልንሰማው ልንፈጽመው የሚገባ ነው።

እንግዲህ እነዚህ የፊተኞች (እሥራኤል ዘሥጋ) ሙሴ ይናገረን እንጂ እግዚአብሔር አይናገረን በማለት ከሚናገራቸው ከእርሱ በመራቃቸው ምክንያት ከቁጣው ካላመለጡ ፤ እኛም ከላይ ከመጣው ቃሉ (ከእርሱ) ፈቀቅ የምንል ከሆነ እንዴት ልናመልጥ እንችላለን ? (ዕብ. 12/25)

ስለዚህ የሚፈርድብንም ይኸው ቃሉ እርሱ ስለሆነ (ዮሐ. 13/24) እምቢ እንዳንል እንጠንቀቅ ። ዓለም በልጁ እንዲድን እንጂ ፤ በዓለም እንዲፈርድ እግዚአብሔር ልጁን ወደ ዓለም አላከውምና ። (ዮሐ. 3/17)

የጌታ የባሕርይ ክብሩ በታቦር ተራራ ላይ ብቻ ተገልጦ የሚቀር አይደለም እንዲሁም ለእያንዳንዱ እንደ ሥራው መጠን ዋጋውን ለመክፈል በክብር በሥልጣን በጌትነትና በኃይል ዳግመኛ ይገለጣል ፤ ስለዚህ በክብሩ በሚገለጥበት ጊዜ እንዳናፍር ለንስሐ የሚገባ ፍሬ ከአሁኑ ማድረግ አለብን ።



www.ethiopianorthodox.org